RAYA FOUNDATION

RAYA FOUNDATION
203 Lexington Avenue
East Lansdowne, PA 19050 USA

# ትህነግ/ህወሓት በራያ ቆቦ የፈፀመው የዘር ፍጅት

የትግራይ ህዝብ ነፃ አዉጭ ግንባር (ትህነግ፣ህወሓት) በራያ አማራዎች ላይ አሰቃቂ ፍጅት ፈፅሟል።

ዋልታ የተባለው ሚዲያ እንዳረጋገጠው ከነሃሴ መጨረሻ ጀምሮ ከ600 በላይ የሚሆኑ ንፁሃን ዜጎች በግፍ ተፈጂተዋል። ጳጉሜ 5፣ 2013 የትህነግ ጦር ከ60 በላይ ያልታጠቁ ዜጎችን ገሎ በጅምላ እንደቀበረ ከጭፍጨፋው አምልጠው የወጡ የአይን እማኞች ተናግረዋል። የጥቃቱ ሰለባዎች የአካባቢው እውቅ ግለሰቦች፣ ወጣት ወንዶች፣ ህፃናትና ሴቶችን ይጨምራል።

ከሰቆቃው የተረፉ እንደመሰከሩት የትህነግ የጥፋት ኃይል ጨለማን ተገን አድርጎ ከከተማ ዉጭ በእርሻ መሬት ላይ የጅምላ ቀብር ያደርጋል። ከዛም አልፎ ከማህበረሰቡ የሃይማኖትና ሞራል ገደብ ውጭ የገደሏቸውን ሰዎች ሬሳ ለቀናት ባደባባይ ለዕይታ በመዘርጋት ህዝቡን ለከፋ የስነ-ልቦና ስቃይ ዳርገዉታል፣ ቤተሰብም ተገቢ የቀብር ስነ-ስርዓት እንዳይፈፅም አድርገዋል። ጥቃቱ ሁለንተናዊ ነው።

የጅምላ ፍጅቱ ለወራት ሲፈፀም ከቆየው የዘረፋ፣ የአስገድዶ መድፈር እና የመሰረተ ልማት ዉድመት የቀጠለ ነው። ሆኖም ኢንተርኔት ስለተቋረጠና የማህበረሰቡ እንቅስቃሴ ስለተገደበ ይህ የሽብር ኃይል ሲፍፅም የቆየውን ግፍ በጊዜ ማወቅ አልተቻለም ነበር።

በአንድ በኩል ሲታይ  ይህ አረመኔ ቡድን በራያ ህዝብ ላይ የፈፀፈው ግፍ በአጋምሳ፣ ጋሊኮማና ጨና ከደረሰው ፍጅት የተለየ አይደለም። ነገር ግን ጉዳዩን በቅርበት ላየ ትህነግ በራያ ህዝብ ላይ ያወረደው የሞት፣ የዉርደት፣ የጥፋትና ችጋር መዓት የዘር ማፅዳት ተግባር ነው ብለን እናምናለን።

የትግራይ ወራሪ ሃይል በራያ የዘር ማፅዳት ወንጀል ለመፈፀም ሁለት መነሻዎች አሉት። አንደኛ ቀድሞ እንደሚታወቀው ትህነግ በአካባቢው ላይ የመሬት ይገባኛል ጥያቄ አለው። ግድያውን የፈፀሙት ቤት ለቤት እየዞሩ፣ አማርኛ ተናጋሪዎች ብቻ መርጠው መሆኑ ደግሞ ህዝቡን ከርስቱ ነቅለው መሬቱን ወደ ግዛታችህው ለማጠቃለል ያየያዙትን ግብ ያሳያል። በቅርቡም ‘ታሪካዊ ግዛታችንን በእጃችን አስገብተናል’ ሲሉ ተደምጠዋል። ሁለተኛ በጎሳ ፖለቲካ ለሰከሩት የትህነግ ወራሪዎች ራያ እንደ ሃሳብ ይኮሰኩሳል። ራያ ትንሿ ኢትዮጵያ ነች፤ የትውልድ ሃረጋቸውን ከተለያየ ዘውግ የሚስቡ ህዝቦች በፍቅርና በሰላም የሚኖሩባት ህብራዊ ምድር! ህልዉናው በልዩነት ላይ በቆመ ለቆመውለዚህ ከይሲ ቡድን  ራያነት ሰላም አይሰጥም። ከዚህ አንጻር ስጋታችን በአካባቢው የደረሰው ጥፋትና ፍጅት ከሞት የተረፉ ምስክሮች ከሚነግሩን የከፋ እንዳይሆን ነው።

እኛም የትህነግ/ህወሓት ሽብር ቡድን በራያ ህዝብ ላይ የፈፀመዉን አሰቃቂ ፍጅት በፅኑ እያወገዝን፣ ይህ የ ጥፋት ኃይል ሌላ ዞር ፍጅት እንዳይፈፅም የፌደራል እና የአማራ ክልል መንግስታት በግዜ ተገቢን እርምጃ እንዲወስዱ ጥሪ እናደርጋለን። የራያ ፋዉንዴሽን ማህበረሰቡን በተቻለው ሁሉ ለመደገፍ ቁርጠኝነቱን ይገልፃል።

በተጨማሪም ዓለም-አቀፍ ማህበረሰቡ (በተለይ ደግሞ የአሜሪካ፣ የብርታኒያ እና የአየርላንድ መንግስታት) የትህነግ/ህወሓት ሽብር ቡድን ባልታጠቁ ዘጎች ላይ የሚፈፅመውን የዘር ፍጅት በግልፅና በቀጥታ እንዲያወግዙና በኢትዮጵያ መንግስት ላይ የሚያደርጉትን ያልተገባ ጫና እንዲያነሱ እንጠይቃለን። ያለ እነዚህ መንግስታት ያልተገደበ ድጋፍ ትህነግ በዚህ ደረጃ ወደለየለት ሽብር እንደማይገባ ግልፅ ነው።

**የራያ ፋዉንዴሽን ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ**

rayafoundation2014@gmail.com

RAYA
FOUNDATION

203 Lexington Avenue
East Lansdowne, PA 19050 USA



መስፍን መኮንን (ቆቦ ት/ት መምህር)



አቶ ሲሳይ ወዳጆ (ነጋዴ)



አቶ ደሳለ ሞላ (አርሶ አደር)




ወጣት አበበ እሸቱ (አርሶ አደር)

rayafoundation2014@gmail.com